OFFICE OF THE STATE
SUPERINTENDENT OF EDUCATION

# የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ለ2025 የበጀት ዓመት ዝቅተኛ ደመወዞች (FY25)

ኖቬምበር 7፣ 2024

## ዳራ

የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ የልጅ እድገት ተቋም ሰራተኞችን ካሳ ለመጨመር ጥቅም ላይ የሚውል የኮሎምቢያ ዲስትሪክት መንግስት ልዩ የገንዘብ ድጋፍ ነው። የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ በዲሲ ምክር ቤት በFY22 የተቋቋመ ሲሆን የሚተገበረው በግዛት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ጽሕፈት ቤት (OSSE) ነው። ኦክቶበር 31 2024 ላይ ከንቲባው የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ክፍያ መጠን አስችኳይ ማስተካከያ 2024ን የፈረሙ ሲሆን ይህም ዝቅተኛውን የደሞዝ መጠን በልጆች እንክብካቤ ውስጥ ለሚሰሩ እና በኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ክፍያ ኢኩዊቲ ውስጥ ተቀጣሪዎች በኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ኢኩዊተብል የክፍያ ግብረሀይል ጥቆማ መሰረት ክፍያ እንዲደረግላቸው የሚያደርግ ነው

አቅራቢው በOSSE የጸደቀ የዝቅተኛ ደመወዝ መስፈርቶች መታለፍ ከሌለው በስተቀር ከቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ የገንዘብ ድጋፎችን የሚያገኙ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች ሁሉም አስተማሪዎች እና ረዳት አስተማሪዎች (በቅድመ ልጅነት ትምህርት ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ደንብ እንደተገለጸው) በስራ ድርሻ እና በትምህርት ማረጋገጫ፣ ለእያንዳንዱ የአስተማሪ አይነት የወጡትን ዝቅተኛ ደመወዞች የሚያሟሉ ወይም ከዚያ የሚበልጡ መደበኛ የሰአት ክፍያዎች ወይም ደመወዞች የሚከፈላቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው። አቅራቢዎች ከዝቅተኛው ደመወዝ በላይ ለመክፈል አይከለከሉም።

## የFY25 ዝቅተኛ ደሞዞች

የ2024 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ መለኪያዎች የአደጋ ጊዜ ማሻሻያ ህግ፣ በቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የካሳ ግብረ ሃይል ምክሮች መሰረት፣ ለFY25 ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርቶች ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ የሚከተሉትን ለውጦች አድርጓል፦

1. **ቢያንስ የልጅ እድገት ተባባሪ (CDA) የትምህርት ማረጋገጫ ለሌላቸው ብቁ አስተማሪዎች ዝቅተኛውን የደመወዝ መስፈርት አስወግዷል።** የOSSE የልጅ እድገት ተቋማት ፈቃድ አሰጣጥ ደንቦች (5-A DCMR ምዕራፍ 1) ለመምህራን፣ ረዳት አስተማሪዎች፣ ተባባሪ የቤት ተንከባካቢዎች፣ የቤት ውስጥ ተንከባካቢዎች እና የተስፋፋ የቤት ውስጥ ተንከባካቢዎች ቢያንስ የ CDA የትምህርት ማረጋገጫ ይጠይቃሉ። በFY25፣ ከ CDA ያነሱ አስተማሪዎች ከአሁን በኋላ በተቋሙ የልጅ እድገት ተቋም (CDF) የደመወዝ መክፈያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት ውስጥ አይካተቱም ምክንያቱም እነዚያ አስተማሪዎች ለስራ ድርሻቸው ዝቅተኛውን የትምህርት መስፈርት አያሟሉም። አንዳንድ አስተማሪዎች በፈቃድ አሰጣጥ ደንቦች ከትምህርት መስፈርቶች ነፃ የሚያደርጋቸውን መታለፎች ቢይዙም፣ እነዚህ መታለፎች የሚፈለገው ዝቅተኛ የትምህርት ማረጋገጫ ላላቸው አስተማሪዎች

ብቻ ማካካሻን ለሚጨምረው የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ አይተገበሩም። የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ከእንግዲህ ለነዚህ አስተማሪዎች ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርቶችን ባያስቀምጥም፣ ተቋማት የ2016 የፍትሃዊ እድል ዝቅተኛ የደመወዝ ህግን እና እና በዲሲ የልጅ እንክብካቤ ድጎማ ፕሮግራም ውስጥ ለሚሳተፉ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች፣ የ2006 የኑሮ ደሞዝ ህግን ጨምሮ ለሁሉም ቀጣሪዎች የሚተገበሩትን የሰራተኛ ደሞዞች እና ሰአታትን በተመለከተ ሌሎች የአካባቢ እና የፌዴራል ህጋዊ መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል። ከጁላይ 1፣ 2024 ጀምሮ፣ የዲስትሪክቱ ዝቅተኛ ደመወዝ እና የኑሮ ደመወዝ ሁለቱም $17.50/በሰዓት ሆነዋል።[1]

2. **በልጅ እድገት ማዕከላት ውስጥ ያሉ መምህራን እና የCDA የትምህርት ማረጋገጫ ያላቸው እና ምንም ተጨማሪ ድህረ ሁለተኛ ዲግሪ የሌላቸውን የተስፋፋ የቤት ውስጥ ተንከባካቢዎችን ዝቅተኛ ደመወዝ ቀንሷል።** በFY25፣ ለእነዚህ አስተማሪዎች ዝቅተኛው የደመወዝ መስፈርት CDA ላላቸው ረዳት መምህራን ከሚጠየቀው ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርት ጋር እኩል ይሆናል። ለመምህሩ እና ለተሰፋፋ የቤት ተንከባካቢ የስራ ድርሻዎች በፈቃድ አሰጣጥ ደንቦች የወጣው ዝቅተኛው የትምህርት መስፈርት በቅድመ ልጅነት ትምህርት (ECE) ወይም ቢያንስ 60 ክሬዲት ሰዓቶች ወይም በማንኛውም የትምህርት ዘርፍ በ ECE ውስጥ ቢያንስ 12 የክሬዲት ሰአታት ያለው ተባባሪ ዲግሪ ነው። ስለዚህ ይህንን ዝቅተኛ መመዘኛ ያላሟሉ አስተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ ካሳ የሚያገኙ ይሆናል። አንዳንድ አስተማሪዎች እና የተስፋፋ የቤት ውስጥ ተንከባካቢዎች በፈቃድ መስጫ ደንቦቹ ውስጥ ካሉት የትምህርት መስፈርቶች ነፃ የሚያደርጋቸውን መታለፎች ቢይዙም፣ እነዚህ መታለፎች የሚፈለገው ዝቅተኛ የትምህርት ማረጋገጫ ላላቸው አስተማሪዎች ብቻ ማካካሻ ለሚጨምረው የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ አይተገበሩም። ይህ ለውጥ ዝቅተኛ የትምህርት መስፈርታቸው CDA የሆነ የቤት ውስጥ ተንከባካቢዎችን <u>አይመለከትም</u>።

3. **የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ የትምህርት ማረጋገጫ መስፈርቶችን በፈቃድ አሰጣጥ ደንቦች (5-A DCMR ምዕራፍ 1) ውስጥ ካለው ዝቅተኛ የትምህርት መስፈርት ጋር አስማምቷል።** ፕሮግራሙ በተፈጠረበት ወቅት በስራ እና በትምህርት ማረጋገጫ የወጡ የFY24 ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርቶች በ OSSE የልጅ እድገት ተቋማት የፈቃድ አሰጣጥ ደንቦች ዝቅተኛ የትምህርት ማረጋገጫ/ዲግሪ መስፈርቶች ላይ የተመሰረቱ ነበሩ። በዲሴምበር 2023፣ OSSE ለመጀመሪያ ደረጃ መምህራን ዝቅተኛ የትምህርት መስፈርቶችን አዘምኗል። አዲሱ ህግ ለቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ የትምህርት ማረጋገጫ መስፈርቶችን ከዘመኑ የፈቃድ አሰጣጥ ደንቦች ጋር ያስማማል (ሠንጠረዥ 1 ይመልከቱ)። እባክዎን ያስተውሉ፣ የፈቃድ አሰጣጥ ለውጦች ለሥራ ድርሻቸው ዝቅተኛውን የትምህርት መስፈርት ያላሟሉ አስተማሪዎች የሚታለፉበት ወይም ለጊዜው ለፈቃድ መስጫ

[1] የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የስራ ስምሪት መምሪያ፣ የደመወዝ-ሰዓት ተገዢነት ቢሮ፣ https://does.dc.gov/service/office-wage-hour-compliance-0።

አላማዎች መስፈርቶችን እንደሚያሟሉ የሚታመንበትን የመታለፎች ዓይነቶችን እና የምስክር ወረቀቶችን ቢያስፋፋም፣ በቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ስር ብቁ የሆነው አስተማሪ የሚያሟላው የካሳ መጠን አስተማሪው በያዛቸው ትክክለኛ የትምህርት ማረጋገጫዎች ላይ የተመሰረተ ነው እና መታለፍ ወይም ቀጣይነት ያለው አገልግሎት ወይም በምዝገባ ላይ የተመሰረተ የምስክር ወረቀት በመያዙ ምክንያት አይጨምርም።።

የFY25 ዝቅተኛ ደሞዞች ከጃንዋሪ 1፣ 2025 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናሉ። አቅራቢዎች በFY25 የመጀመሪያ ሩብ አመት የሽልማት ክፍያ መቀበላቸውን ተከትሎ ብቁ ለሆኑ አስተማሪዎች ዝቅተኛውን የደመወዝ መስፈርቶች እንዲያሟሉ ይጠበቃል።

**ሰንጠረዥ 1. የ CDF የደሞዝ መክፈያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማቶችን ለሚቀበሉ የልጅ እድገት ተቋማት ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርቶች፣ FY25**

| የስራ ድርሻ | የትምህርት ማረጋገጫዎች | የFY24 ዝቅተኛ ደሞዞች (አመታዊ ደመወዝ) | የFY24 ዝቅተኛ ደሞዞች (የሰዐት ደመወዝ) |
|---|---|---|---|
| • ረዳት አስተማሪ<br>• ተባባሪ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ | CDA ወይም ተመጣጣኝ | $51,006 | $24.52/ሰአት |
| | ተባባሪ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ ወይም በማንኛውም የትምህርት መስክ የ 60 ሰዓታት የኮሌጅ-ደረጃ ኮርስ ስራ | $54,262 | $26.09/ሰአት |
| • መሪ መምህር<br>• የተስፋፋ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ | CDA ወይም ተመጣጣኝ | $51,006 | $24.52/ሰአት |
| • የቤት ውስጥ ተንከባካቢ | CDA ወይም ተመጣጣኝ | $54,262 | $26.09/ሰአት |
| • መሪ መምህር<br>• የቤት ውስጥ ተንከባካቢ | በECE ውስጥ ተባባሪ ዲግሪ፤ በECE ውስጥ ከ12 ክሬዲት ሰአታት የበለጠ ወይም እኩል የሆነ ተባባሪ ዲግሪ፤ ወይም በECE ውስጥ ከ12 ክሬዲት ሰአታት የበለጠ ወይም | $63,838 | $30.69/ሰአት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • **የተስፋፋ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ** | እኩል የሆነ የ60 ሰአታት የኮሌጅ-ደረጃ ኮርስ ስራ | | |
| | በ ECE የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ ወይም በECE ውስጥ ከ12 ክሬዲት ሰአታት የበለጠ ወይም እኩል የሆነ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ | $75,103 | $36.11/ሰአት |

የCDF የደመወዝ መክፈያ ቀመር የገንዘብ ድጋፎችን ያልተቀበሉ ተቋማት ለሰራተኞቻቸው የሚፈለገውን ዝቅተኛ ደመወዝዎች እንዲከፍሉ አይገደዱም ነገር ግን የ2016 የፍትሃዊ እድል ዝቅተኛ የደሞዝ ህግ እና በዲስትሪክቱ የልጅ እንክብካቤ ድጎማ ፕሮግራም ውስጥ ለሚሳተፉ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች፣ የ2006 የኑሮ ደሞዝ ህግን ጨምሮ ከሌሎች የዲስትሪክት እና/ወይም የፌደራል ህጎች እና ለሁሉም ቀጣሪዎች ተፈጻሚ የሚሆኑ የሰራተኛ ደመወዞችን እና ሰዐታትን የሚመለከቱ መስፈርቶችን ማክበር አለባቸው።